# ምስቅልቅል

ህሊና ተገፎ ሲጣል፣
አለም ሆና እርፍ ምስቅልቅል።

የገነት ምድር ቢላትም፣
ሲኦል ሆና ቁጭ ኤደንም።

እግዚአብሔር ከሕዝብ ሲርቅ፣
ፈልስጣ ተንሰራፍቶ ቁጭ።

በግ ጠብቅ ቢለው እየሱስ፣
ቀበሮ ወዶ ቁጭ ጳውሎስ።

ጴጥሮስ ተወግዞ በቅዬው፣
ጲላጦስ ሆነ አጥማቂው።

አለልክ ጠግቦ ሲያገሳ፣
አሳማ ሞትን እረሳ!

የከርስ ወርዱ ሲሰፋ፣
ልቡና ብን ብሎ ጠፋ።

ጽንስ ሺል አፍነን ገለን፣
ውርጃውን ታቅፈን አለን።

ብዙዎች በችጋር ሲያልቁ፣
ጥቂቶች በቁንጣን ሳቁ።

ተበዳይ ዘብጥያ ሲወርድ፣
በዳዩ ስልጣን ላይ ቁጢጥ።

ሚች ሲወርድ ወደ መቃብር፣
ገዳዩ ጉልት ከወንበር።

ዝሆኑ ገጥሞ ሲታገል፣
ሳሩ ደቀቀ በመሐል።

አውሮጳ ፍቅር ሲቋደስ፣
አፍሪካ በጥርስ ይናከስ።

ጀርመኒ ግንቡን ሲንደው፣
“ጦቢያ” ግን እየካበች ነው።

ክልልን እምቢ ሲል ሰው፣
ከትሞት እርፍ አውሬው።

የሌሎች መቀነት ሲጠብቅ፣
ድንቅነሽ ቀሚሷ ውልቅ።

ኮሎንበስ አለምን ሲያደርስ፣
በክልል ታስሯል አዳምስ።

ጆርጅዬ ግዛት ሲያሰፋ፣
“አቤ”ዋ ያዘ ከተፋ።

የፋኖ ምንጮ ሲነጥፍ፣
ባንዳ ግን ወረደ እንደ ጎርፍ።

ህሊና ተገፎ ሲጣል፣
አለም ሆና እርፍ ምስቅልቅል።

እህ…!

ምስቅልቅል!!!

ምስቅልቅል!!

ምስቅልቅል!

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ነሐሴ ሁለት ሺህ ዓ.ም.